የሰ/መ/ቁ. 54632

29/09/2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ራውዳ ሙሜ - ጠበቃ አበራ ማረኝ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አምባሳደር አብደላ አብዱራህማን - ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት ክርክር ሲሆን የተጀመረው በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ባቀረበው ክስ ነው፡፡ ቀርቦ የነበረው ክስ በአጭሩ በመካከላችን የነበረው ጋብቻ በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በመዝ.ቁ. 64296 ሚያዝያ 30 ቀን 1998 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሣኔ ፈርሷል፡፡ የጋራ ንብረት ክፍፍልን በተመለከተ ተከሳሽ ካናዳ ቶሮንቶ ከተማ 4725 የቤት ቁጥር 1614 የሆነውን ኮንዶምኒየም ተከሳሽ እንዲወስዱና በአ/አበባ ን/ስል/ላ/ክ/ከተማ ቀበሌ 05 የቤት ቁጥር 1775 የሆነውን ደግሞ ከሣሽ እንድወስድ የሚል ሃሳብ አቅርቤ ተከሳሽ ከሣሽ ያልተሳተፍኩበትን በካናዳ ፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ በማቅረብ ለፍ/ቤቱ በማመልከታቸው በከፍተኛው ፍ/ቤት እንዲታይ የሚል ውሣኔ በመስጠቱና በይግባኝም በመጽናቱ የቀረበ ነው፡፡ የተባለው የካናዳ ፍ/ቤት ውሣኔ ከሳሽ በሌለበት የተሰጠ የጋራ ንብረቱን በሙሉ ለአንደኛ ወገን የሚሰጥና የካናዳን ሕገ መንግስት የሚፃረርና ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ከላይ ባቀረብኩት የክፍፍል ሃሳብ መሰረት እንዲወሰን በሚል ጠይቋል፡፡

ክሱ ለተከሳሽ ደርሶ በሰጡት መልስ የከሳሽና የተከሳሽ ጋብቻ ከመፍረሱም በላይ የካናዳ ፍ/ቤት ሰኔ 23 ቀን 1998 ዓ.ም በዋለው ችሎት በቀረበበት የንብረት ክርክር የካናዳውም ሆነ በአ/አበባ የሚገኘው ቤት ለተከሳሽ እንዲሰጥ የተባለ በመሆኑ አሁን የቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 5 መሠረት ተቀባይነት የለውም በማለት የካናዳ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ መሠረት አፈፃፀም የማቅረብ መብቴ ተጠብቆ የደረሰው ኪሣራ እንዲከፈለኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤት ከላይ እንደተመለከተው ከክርክር በኋላ የፍች ውጤት መታየት የሚገባው ጋብቻ በተመሰረተበት ሀገር ህግ በመሆኑ እና በካናዳ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ሁሉንም ንብረት ለአንድ ወገን ብቻ የተደረገ በመሆኑ በኢትዮጵያ ህገ መንግስት አንቀጽ 34 መሠረት ባልና ሚስት በፍች ውጤት ላይ ያላቸውን እኩል ህገ መንግስታዊ መብት የሚነካ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም

በማለት እኩል እንዲከፋፈሉ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርዱ ቤቱም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 337 መሠረት አጽንቷል፡፡

አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካች በጠበቃቸው አማካኝነት መጋቢት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በ2 ገጽ በፃፉት ማመልከቻ ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡ የቅሬታው ፍሬ ሃሳብ በዚህ ጉዳይ ቀድሞ በካናዳ ፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ እያለ በማለፍ የበታች ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ እንድሻርልን የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ በጠበቃ በኩል ጥቅምት 29 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ 2 ገጽ መልስ በካናዳ ተሰጠ የተባለው ፍርድ ያልተከራከርኩበትና የአንደኛውን ተከራካሪ ወገን መብት የሚስጥ መሆኑን ፍ/ቤቱ በመገንዘብ ውድቅ ያደረገው በመሆኑ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ እንዲፀና በማለት ተከራክሯል፡፡ የመልስ መልስም ቀርቧል፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ክርክር አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም በግራ ቀኙ የተነሱትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘበ መርምሮታል፡፡ በዚሁ መሠረት በግራ ቀኙ መካከል ያለው ጋብቻ በፍርድ ቤት ውሣኔ መፍረስ ተከትሎ ያለው የንብረት ክፍፍል ክስ ቀድሞ በፍርድ ያለቀ ጉዳይ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ተይዞ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚሁ መሠረት ይሄንን ጉዳይ ስንመረምረው አመልካች ቀድሞ በፍርድ አልቋል የሚሉት በካናዳ ፍርድ ቤት ተሰጠ የተባለውና በኢትዮጵያም ሆነ በካናዳ የሚገኙትን መኖሪያ ቤቶች ለአመልካች ወስኗል የተባለውን ፍርድ ነው፡፡

አንድ የውጭ ሃገር ፍርድ ከአገራችን የፍትሐብሔር ስነ ሥርዓት እይታ አኳያ ሲታይ የክሱ መጀመር ወይም ከተወሰነ በኂላ ለአፈፃፀም ቢቀርቡ ያላቸው ተቀባይነት በተመለከተ አግባብነት ያላቸው የሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 8/2/ እና በውጭ አገር የተሰጠ ፍርድ ወይም ብይን ስለሚፈፀምበት ሁኔታ የሚደነግገው ከአንቀጽ 456 እስከ 461 ሥር የተደነገጉት ናቸው፡፡ የመጀመሪያውን አንቀጽ ማለትም አንቀጽ 8/2/ በምናይበት ጊዜ በውጭ አገር ክስ መጀመሩ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተቀብሎ ከመመልከት እንደማያግደው የሚያመለክት በመሆኑ በዚሁ እናልፈዋለን፡፡ ከላይ በሁለተኛ ደረጃ የተመለከቱትን የህግ ድንጋጌዎች በምናይበት ጊዜ አንድ የውጭ ሃገር ፍርድ የመጨረሻ ውሣኔ ተሰጥቶበት መቅረቡ ብቻ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ሊያስገኝለት የማይቻል ስለመሆኑና የተለያዩ መመዘኛዎችን ማሟላት እንዳለበት ይደነግጋሉ፡፡ የተመለከተው ፍርድ ደግሞ በሥነ ሥርዓት ሕጉ ላይ የተጠቀሱትን መመዘኛዎች ያሟላል ወይስ አያሟላም ማለት ደግሞ የሚቻለው የተሰጠው ፍርድ ይጠቅመኛል ወይም መብት ያጐናጽፈኛል ባይ የአፈፃፀም ማመልከቻ ከላይ በተጠቀሱት የሥነ ሥርዓት ሕጐች መሠረት ብታቀርብ ኖር እንጂ ለቀረበባቸው ክስ እንደመከራከሪያ በማቅረብ አይደለም፡፡

በመሆኑም በካናዳ ፍርድ ቤት ተሰጠ የተባለው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 456 እስከ 416 በተመለከተው አግባብ ተቀባይነቱ ለፍርድ ቤት ቀርቦ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካችም ይሄንን ባለፍፀሙበት ሁኔታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 5 መሠረት የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ ጉዳይ ነው በማለት የቀረቡት መከራከሪያ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ከዚህ አኳያ የተነሳውን ተቃውሞ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለመሆነም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 51738 የካቲት 17 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 71195 ጥቅምት 30 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ ያላቸውን የጋራ ንብረት በኢትዮጵያ የፌዴራል ቤተሰብ ህግ መሠረት እኩል ይካፈሉ መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በግራ ቀኙ ላይ በዚህ ችሎት ለደረሰው ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡